# ትንቢት አለ መሰል

ዛፍና ኩሬ ላይ ፣ ተጽፎ የሚያየው ፣ የዋቄ ዳዊቱ
በየመድረኩ ላይ ፣ የሚያቀነቅነው ፣ ኢሬቻ ሃይማኖቱ
ባህሌ ኩራቴ ፣ እያለ ቢያወራም ፣ የፈሰሰ ሃሞቱ
ከሌላው አንሳለሁ ፣ በማለት እራሱን ፣ ያሳመነ ከንቱ
ድካሙ እንደሆነ ፣ ጠልፎ የሚጥለው ፣ የገዛ ጠላቱ
አልገባ ስላለው ፣ ምክንያት ያበዛል ፣ ሁሌም ለድክመቱ
ሽቀብ አይራመድ ፣ ሁሌም የሱ ምርጫ ፣ ወደ ቁልቁለቱ
በጭፍን የሚሮጥ ፣ ከታሪክ አይማር ፣ ውርደቱ ኩራቱ
ማላዘን አይደክመው ፣ ውሃ እንደወቀጠ ፣ ይሄው ሃምሳ ዓመቱ ።

በሚያሰለች ዜማ ፣ እያለቃቀሱ ፣ ዘወትር እሪታ
ስንኩል አረማመድ ፣ የተወላገደ ፣ ሽውራራ እይታ
ከደዌዎች ክፉ ፣ ዝቅተኛ ስሜት ፣ የማይድን በሽታ
ሃኪም አያድነው ፣ ጸበል አይፈውሰው ፣ የጠንቋይ ቱፍታ
ሞት ካልገላገለው ፣ የሻገተ አይምሮ ፣ ታስሯል ላይፈታ
የጠባቦች መንጋ ፣ በሃሳብ ልዕልና ፣ አንሶ የተመታ
ዝንተ ዓለም ይኖራል ፣ እንዳለቃቀሰ ፣ ሲያሰማ አቤቱታ ።

አምና ላይ የቆሙ ፣ ዛሬን የዘነጉ ፣ ነገ አይታያቸው
ከፍ ብታደርገው ፣ ዝቅ ብሎ ማሰብ ፣ ህመም የሆናቸው
በልተው የማይጠግቡ ፣ አንኳን አጉርሰኸው ፣ ቢበሉ ባይናቸው
ዛሬም አድሮ ቃሪያ ፣ ነገም ታጥቦ ጭቃ ፣ ትምህርት አይገራቸው
ልክ እንደ ግመል ሽንት ፣ ሁሌም ወደኋላ ፣ የሆነ ምርጫቸው
መቼም አይማሩም ፣ በፈለጉት ቋንቋ ፣ ካላናገርካቸው ።

ነፍጠኛው ባጸናት ፣ ተምሮም ደንቆሮ ፣ ድፍን ቅሉ በዝቶ
እኔ ከዚህ ዘር ነኝ ፣ እሱ ከዚያ ዘር ነው ፣ የሚል መርዝ ዘርቶ
በጥላቻ ትርክት ፣ ወንድም ከወንድሙ ፣ ለማራቅ ለይቶ
ምናብ በፈጠረው ፣ በጅ የማይዳሰስ ፣ ጠላት አዘጋጅቶ
ሲባንን ይኖራል ፣ እድሜ ዘላለሙን ፣ አያድር ተኝቶ
በሰላም እንዳይኖር ፣ የታሪክ ቡቱቶ ፣ ትርክቱን ደርቶ
ስልጣን መውጫ ፣ ደሃን ይማግዳል፣ ሊነግሥ አመካኝቶ ።

በዜጋ ትከሻ ፣ ለዘመናት ነግሶ ፣ ተጭኖ የኖረ
አፋኝና ገዳይ ፣ ፋሽስታዊው ስርዓት ፣ ስንል ተቀበረ
በማሰር በመግደል ፣ ጠብደል አሽከር ሆኖ ፣ ሲኖር የነበረ
እሱ ታግሎ ሳይሆን ፣ ሌሎች በሞቱበት ፣ ስልጣን የተቸረ
ካፍንጫው አርቆ ፣ ማየት የተሳነው ፣ ጭፍን የታወረ
ስራ ፈት ቦዘኔ ፣ መንጋ እያሰማራ ፣ አገር ተሸበረ
ከሰላሳው ዓመት ፣ ያንዱ ዓመት መከራ ፣ በእጥፍ ጨመረ
ትንቢት አለ መሰል ፣ እኛ ያልሰማነው ፣ ጥንት የተነገረ
ሌሎች ያመሱት ሕዝብ ፣ ባዲሱ ተረኛ ፣ ተቆላና አረረ ።

ታዛቢው

October 7, 2019